


# ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ፣ግብረ

" ሚስጥሩ ቴአትር መድረክ ቴአትር ዝግጅት አላባዊያን ትንተና"

በ

አስናቀ አለማየሁ

# የማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮለጅ የቴአትር ጥበባት ት|ክፍል ለባችለር ኦፍ አርት ድግሪ ማሟያነት የተሰራ

ግንቦት 2015 ዓ.ም

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ፣ግብረ

"ሚስጥሩ ቴአትር መድረክ ዝግጅት አላባዊያን ትንተና"

በ

አሰቀና አለማየሁ

የጥናቱ አማካሪ

መምህር ሽኩር ናስር

# የማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮለጅ የቴአትር ጥበባት ት|ክፍል ለባችለር አፍ አርት ድግሪ ማሟያነት የተሰራ

ግንቦት 2015 ዓ.ም

## የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ መሰርት ድጋፍ የተደረጋለት መሆነን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው----------

ፍርማ----------

ይህ ጥናት በተማሪ አሰናቀ አለማየሁ "ሚስጥሩ ቴአትር ከመድረክ ቴአትር ዝግጅት አላባውያን አንፃር መተንተን" የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፁሁፍ ሲሆን የዩንቨርስቲውን ትራት ደረጃ የሟላና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀበይናት መሆኑን ያገኘ ማረጋገጫ ነው።

ፈታኝ አንድ----------ፍርማ----------

ፈታኝ ሁለት----------ፍርማ----------

ቀን----------

# ምስጋና

በመጀመሪያ ከጀማሬ እስከ ፍፃሜ ያልተለየኝ ለድንግል ማርያም ልጅ ለእየሱስ ክርስቶስ በልጅነት አንደበት ምስጋናየን አቀርባለሁ። በመከጣል በሀሳብም በሚቅሪም ስያግዝ ያነበረውን ለአማካሪ መምህር ሽኩር ናስር ምስጋናየን አቀርባለሁ። በመጨረሻም ዘወትር በሀሳብም በሌሎችም አገዙኝ የነባሩ የክላስ ጓደኞቼ እና ሚስጥሩ ቱአትር ዝግጅቱ አሰታባባሪ ለንጉሴ በይሌ ምስጋናየን አቀርባለሁ።

# አበርክቶ

ዘወትር ሲከፈኝ እያፅናኑ ደስተየን እያበዙ ከገንዘብ አሰከ ጉልበታቸው ከልጅነት እሰከ ዛሬ ላልተለዩኝ ለወድ እናቴ ለማሚ በላይ እና ለወንድሜ አበበ አለማየሁ ይሁንልኝ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ሚስጥሩ ቴአትር ከዝግጅት አላባዊያን ተንትኖ የቀርብ ነው።ሰለሆንም አጥኚው ሚስጥሩ ቴአትር ከዝግጅት አላባዊያን አንፃር ተንትኖ አቅርቧል። አጥኚው ይህን ጥናት ከግብ ለማደረግ መነሻ የሆንውን ተውኔቱን ደጋግሞ በማንበብ ፣ ቴአትር በሚቀርብበት ሰዓት ቴአትር በማየት እና ሌሎችም ተውኔቶች እና በምርምር ዙሪያ የተፃፉ መፅሃፍትን አመቃኝነት ከዝግጅት አላባውያን ትንተኖ አቅርቧል። በነዚህም መፅሃፍት ተመርኩዞ እና ቴአትሩ በማየት አጠቀላይ ሚጥስሩ ቴአትር ከዝግጅት አላባዊያን ተንትኖ በጥናቱ ውስጥ ተንካራ እና ደካማ ጎኖችን አስፍሯል።

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ..... II

አበርክቶ ..... III

አጠቃሎ ..... IV

ማውጫ ..... V

ምዕራፍ አንድ ..... 1

1. መግቢያ ..... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 2

1.2. የጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ..... 2

1.3. የጥናቱ አላማ ..... 2

1.3.1. የጥናቱ አብይ አላማ ..... 3

1.3.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ ..... 3

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 3

1.5 የጥናቱ ወሰን ..... 4

1.6.1. የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..... 4

1.6.2 ምልከታ (observation) ..... 4

1.6.3 ቃለ መጠይቅ (interview) ..... 5

1.6.4. መዛግብት ..... 5

1.7 የጥናቱ ቅርፅ (አወቃቀር) ..... 5

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮዎች እና መፍትሄዎቻቸው ..... 6

ምዕራፍ ሁለት ..... 7

2.1 ንድፍ ሀሳብ ቅኝት ..... 7
2.1.1 የተውኔት ምንነት ..... 7
2.1.2 የአጭር ጊዜ ተውኔት ..... 7
2.1.3 የሙሉ ጊዜ ተውኔት ..... 8
2.2 የቴአትር ዝግጅት ..... 8
2.3 የአዘጋጅ ምንነት ..... 8
2 3.1 በዝግጅት ወቅት የአዘጋጅ ሀላፊነት ..... 9
2.4 የዝግጅት አላባውያን ..... 10
2.4.1 የመድረክ ግንባታ ..... 10
2.4.2 ቁሳቁስ ..... 10
2.4.3 መብራት ..... 10
2.4.4 አልባሳት ..... 11
2.4.5 ገፅ-ቅብ ..... 11
2.4.6 ግብዐተ-ድምፅ ..... 12
2.5 የተዛማች ጥናታዊ ዕሁፍ ቅኝት ..... 12
ምዕራፍ ሶስት ..... 14
3 የመረጃ ትንተና ..... 14
3.1 ሚስጥሩ ቴአትር ጭምቅ ታሪክ ..... 14
3.2 የዝግጅት ወቅት ..... 15
3.3 ሚስጥሩ ቴአትር ቅርፃዊ እና ይዘታዊ አቀራረበ ..... 16
3.3.1 ቅርፃዊ አቀራረብ ..... 16
3.3.2 ይዘታዊ አቀራረብ ..... 16
3.4 ተውኔታዊ ድርጊያው ..... 17
3.5 ድባብ ..... 17
3.6 የዝግጅት አላባውያን ትንተና ..... 17

3.6.1 መድረክ ግንባታ ..... 17
3.6.2 ግብዓተድምፅ ..... 18
3.6.3 መብራት ..... 18
3.6.4 ቁሳቁስ ..... 19
3.6.5 አልባሳት ..... 19
3.6.6 ገፅ ቅብ ..... 20
ምዕራፍ አራት ..... 21
4 ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ ..... 21
4.1 ማጠቃለያ ..... 21
4.2 የመፍትሄ ሀሳብ ..... 21
ዋቢ-መፅሃፍት ..... 22

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ቴአትር የሰው ልጆችን በህይወት ዘመናቸው የሚያጋጥማቸው ከጊዜ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን በተለያዩ መልኩ መድረክ ላይ የሚቀርቡበት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው። ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ስነ ልቦናዊ አስተሳሰቦችን በአንድ በተወሰነ ቦታ እና ጊዜ በመድረክ በማሳየት በሰዎች አመለካከት ለውጥ የሚያመጣ ጥበብ ነው። ቴአትር ብዙ የጥበብ ዘርፎዎች በሥሩ ያቀፈ የጥበብ አባት ወይንም ጥላ ነው ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል የቴአትር ዝግጅት በአንድ የቴአትር ስራ ውስጥ ከመጀመሪያው የንባብ ልምምድ አንስቶ እስከ ተውኔቱ የሚቀርብበት ጊዜ ድረስ ያለው ሂደት ሲሆን ለዝግጅት የሚረዱ መድረክ ግንባታ፣ መብራት፣ ግብዓተ-ድምፅ፣ቁሳቁስ እና አልባሳት በማካተት ተውኔቱ ህይወት ዘርቶ በመድረክ ላይ እንዲቀርብ የሚረዱ ናቸው። በቴአትር ተውኔቶች አማካኝነት የሰዉ ልጆች የዕለት-ተለት ኑሮአቸውን በመድረክ ላይ በማምጣት፤ ከሌሎች የኪነ-ጥበብ ዘርፎች የሚለይበትም በቀጥታ ያለምንም ድልድይ ከተመልካች ጋር ስለሚያገናኝ ከፍተኛ ሃይል ይኖረዋል።

ተውኔት የራሱ ባህርያት ያሉት የስነ-ፅሁፍ አይነት ሲሆን እንደሌሎቹ ስነ-ፅሁፎች የማህበረሰብን ልዩ ልዩ ገፅታም ያንፀባርቃል። የተመረጡትን የማህበረሰብ ገፅታ በማሰየት ረገድ ከሌሎች የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች የሚጋራቸው የኪነ ጥበብ ባህርያት ቢኖሩትም ገና ከመነሻው ሃሳቦችን ሆነ ሁነቶችን ተዋናይን እንደ አንድ መሳሪያ መጠቀሙ ከሌሎች ባህሪያት ልዩ ያደርገዋል። ተውኔት በደራሲው ወይም በፀሃፊ ተውኔቱ በተመረጠ ቦታ እና ጊዜ ክልል በዲርጊት ወደ መድረክ ስለሚያቀርብ ከቀሩት የስነ ፅሁፍ አይነቶች ይበልጥ ለሰሜታችን ቅርበት አለው ። ገፅ ባህርያቱን በመድረክ ላይ በማምጣት ራሳችንን እንድንመረምር ፣ ማንነታችን እንደናውቅ በአጠቃላይ የምንኖረውን ህይወት ከበፊቱ ይበልጥ እንድናጤን የማድረግ አቅም ያለው የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው።ሚስጥሩ ቴአትር አጠቃላይ ዝግጅት አላባውያን መብራት ስርጭት፣ አልባሳት፣ ገፅ ቅብ፣ንብኣተ-ድምፅ እና ቁሳቁስ ላይ በውስጡ የነበረው ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች መግለጽ ነው።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በሀገራችን ቴአትር ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ዘዉግ ፣ ጭብጥ እና በተለያዩ የአቀራረብ አይነት ተመልካችን እያዝናና እና እያሰተማረ ሲቀርብ ኖሯል። ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደ ተጀመረ እና በሃይማኖት ተቋማት እንደ ነበረም ይገልጻል። የቴአትር ዝግጅት አንድ ፀሃፊ ተውኔት ያዘጋጀውን ተውኔት በመድረክ ላይ በተዋንያን፣ በአዘጋጁ እንዲሁም በተለያዩ ቴክኒካል ባለሙያዎች አማካኝነት መድረክ ላይ የሚቀርብበት ሂደት ነው።

ደበበ ሰይፉ ሰለዝግጅት አስፈላጊነት አንዲህ ብለዋል። ***" የቴአትር ጥበብ ምሉዕ የሚሆነው መደበኛ መልኩንም አገኘ የሚባለው በመድረክ ዝግጅት አማኝነት ነው።"(1973÷14)***

አጥኝው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ያነሳሳዉ ምክንያት የመጀመሪያው ቴአትሩ በሚዘጋጅበት ወቅት ላይ የነበረውን ጠንካራ እና ደካማ ጎኑ ምን እንደነበር ለመገምገም በማሰቡ እና ቴአትሩ በሚቀርብበት ሰዓት የተጠቀመውን ቴክኒካል ግብዓቶችንአ በመመልከት የነበረውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለማወቅ በማሰቡ ነው።

በሚስጥሩ ቴአትር ከዝግጅት አላባዊያን አንፃር ከተሰራው ጥናታዊ ፅሁፎችን በማንበብ በውስጡ ያለውን ችግር ወደፊት መፍትሄ እንዲገኝበት ለማድረግ ነው።

## 1.2. የጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- ✓ የሚስጥሩ ተዉኔት የቴክኒካል ግብአት አጠቃቀም ምን ይመስላል? የነበረው ጠንካራ እና ደካማ ጎን ምን ነበር?
- ✓ የሚስጥሩ ተዉኔት አጠቃላይ የዝግጂት ወቅት ማለትም ከንባብ ጀምሮ ቴአትሩ እስከሚቀርብበት ድረስ የነበረው ዝግጂት ምን ይመስላል? የማሉትን ሃሳቦች ያነሰል።

## 1.3. የጥናቱ አላማ

ይህ ጥንታዊ ፅሁፍ በውስጡ አብይ እና ንዑስ አላማዎችን አካቶ ይዟል።

### 1.3.1. የጥናቱ አብይ አላማ

የዚህ ጥናት "ሚስጥሩ" የተሰኘው ቴአትር ከመድረክ የቴአትር ዝግጅት አላባዊያን አንፃር መተንተን ላይ ብቻ ያተኩራል።

### 1.3.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ

- ሚስጥሩ ቴአትር በዝግጅት ሂደት ውስጥ የመድረክ ግንባታ፣ መብራት፣ ግብዓተ-ድምፅ፣ቁሳቁስ፣ አልባሳትን መተንተን።
- የቴአትሩ አዘጋጅ በዝግጅት ሂደት ውስጥ የነበረውን ሚና እና የገጠሙትን ተግዳሮቶችን ማሳወቅ።
- የቴአትር አዘጋጅ በዝግጅት ሂደት ዉስጥ ያለዉን ሚና ማሳወቅ።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጠቀሜታ ሰለ" ሚስጥሩ "ቴአትር ሰፊ ማብራሪያ በመሰጠት፤ ተደራስያን እና በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች እንዲሁም ተማሪዎች ስለ ቴአትሩ ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲያገኙ ያስችላል። ሌላው የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጠቀሜታ ቴአትር ማዘጋጀት ለሚፈልጉ ሰዎች ምን ምን ዝግጂት ማድረግ ሊኖርባቸው እንደሚችል ጥቁምታ ይሰጣል። አንድ ቴአትር በሚዘጋጅበት ሰዓት የሚያስፈልጉ አጠቃላይ ቴክኒካል ነገሮች ምን እንደሆኑ ያሳዉቃል።ሚስጥሩ ተዉኔት ከመድረክ ዝግጂት አንፃር ሲተነተን የነበረዉን ተንካራ እና ደካማ ጎኑን በመለየት ለሌሎች አዘጋጆች ከስህተቱ እንዲማሩ እና የነበረዉን ጠንካራ ጎን እንዲያስቀጥሉ ያስችላል። ከመድረክ ዝግጂት አንፃር እና መሰል ጥናታዊ ፅሁፎች ዙሪያ ለሚሰሩ እንደ ግብአትነት ያገለግላል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ሚስጥሩ ቴአትር ከመድረክ ዝግጅት አላባዊያን አንፃር መተንተን ላይ ብቻ ያተኩራል።

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

አጥኝው ይሄን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ገላጭ የምርምር አይነትን የተከተለ ነው። አለም እሸቱ " መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ"ላይ እንደገለፀው

*ገላጭ ምርምር ገለፃን፣ትንታኔንና አተረጓጎም መሰረት የሚያደርግ ሲሆን በሁለት ተለዋዋጮች መካካል የሚኖረውን ተዛምዶ እያወዳደረ እና እያነፃፀረ ሊመለከት ይችላል። በዚህ ሂደት ውስጥ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰብ ሲሆን ትኩረቱ ግን የአንዱን ተጨባጭ ሁኔታትክክለኛ ባህርይ መግለጽ ወይም ማሳወቅ ይሆናል። (1994÷149*

### 1.6.1. የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ማንኛውም ጥናታዊ ፅሁፍ የጥናቱ አይነት እና ጥናቱ ለመስራት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አለው።

አጥኝው ይህን ጥናታዊ ፅሁፎችን ለመስራት የተጠቀመበት መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ፣ቃለ መጠይቅ እና መዛግብት ናቸው።

### 1.6.2 ምልከታ (observation)

አለም እሸቱ "መሠረታዊ የምርምር ዘገባ አፃፃፍ" ላይ ስለ ምልከታ እንዲህ አስቀምጧል

ምልከታ በአለፍ አገደም አይተን የምናልፈው ጉዳይ ሳይሆን በቅድሚያ ለታቀደ መሰረታዊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሲባል የሚከናወን ትኩረትንና ምርምርን የሚጋብዝ መረጃ የማሰባሰብያ ስልት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ በቂ ጊዜ ወስዶ መመልከት

የተመለከቱትንም ሳይዘገዩ ወዲያውኑ መዝግቦ ማስቀረት የተያያዙ ክንውኖች ይሆናል። 1994፣63

በተጨማሪም ምልከታ የአንድን ድርጊት ወይንም ክንዋኔ ደካማ እና ጠንካራ ጎኖችን ለመለየት የሚጠቅም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው።

### 1.6.3 ቃለ መጠይቅ (interview)

አለም እሸቱ "መሠረታዊ የምርምር ዘገባ አፃፃፍ" በተሰኘው መፅሐፍ ላይ እንዲህ በማለት ተቀምጧል። ቃለ መጠይቅ ተጠያቂው ከጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝቶ በፅሁፍ ሳይሆን በቃል መልልስ የሚሰጥበት ሂደት ነው።(1994፣64)

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ አጥኚው "ሚስጥሩ" የተሰኘው ቴአትር ደራሲ እና አዘጋጅን የተለያዩ ለጥናቱ የሚያግዙ መረጃዎችን ለማግኘት ቃለ መጠይቅ በማድረግ ሚሰበሰብ ነው።

### 1.6.4. መዛግብት

መዛግብት ማለት በፅሁፍ መልክ ከቤተ መፅሃፍት፣ቤተ መዛግብት ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው። ሰለዚህ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ አጥኚው ለጥናቱ ይረዳሉ ተብለው የሚታመንባቸው ዋቢ መፅሀፍትን በማንበብ እና የተለያዩ ተመራቂ ተማሪዎች የሰሩን ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ፅሁፎችን በማንበብ ነው።

## 1.7 የጥናቱ ቅርፅ (አወቃቀር)

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በአራት ዋና ዋና ምዕራፎችን የተከፈለ ነው። በምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣የጥናቱ ደራ ፣የጥናቱ አላማ ፣ የጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናን ውስን፣ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ አወቃቀር እና የጥናቱ ወቅት ያገጠሙ ችግሮች አካቷል። በምዕራፍ ሁለት ንድፍ ሀሳብ እና የተዛማች ስራዎች ቅኝት ይዟል። በምዕራፍ ሶስት" ሚስጥሩ" ቴአትር ከመድረክ ዝግጅት አላባውያን አንፃር መረጃ መተንተን ያትታል። በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ፣የመፍትሄ ሀሳቦች እና ዋቢ- መፅሃፍትን አጣቃሏል።

## 1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮዎች እና መፍትሄዎቻቸው

አጥኚው ጥናቱ በሚያጠነበት ወቅት ሰለዝግጅት አላባዊያን አንፃር የሚያብራሩ መፅሃፍትን በሚፈልገው መጠን ማግኘት አልቻለም ነበር።ይህንን የመፅሃፍት ችግር ከግቢው መፅሃፍት ቤት ውጭ በሆኑ ልዩ ልዩ የመረጃ ቦታዎች በማፈላለግ ተጠቅሟል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 ንድፍ ሀሳብ ቅኝት

### 2.1.1 የተውኔት ምንነት

ተውኔት የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገፅዎች መሰርት በማድረግ በተዋንያን አማካኝነት መድረክ ላይ የሚያቀርብ የሰነ ጥበብ ዘርፍ ነው። ዘሪሁን አስፋ የሰነ ፅሁፍ መሰረታዊ ላይ አንዲህ ይገልፀዋል።

ተውኔት በሰው ልጅ አኗኗር ጠንካራ ሂሰ የሚስጥ በአንድ ሁኔታ ውስጥ በሚቀረፅ ገፅ ባህርያት አማካኝነት የሚከሰት ሰዋዊ ሁኔታ ገልፆ ከአእምሮ የማይጣፋ አሳማኝነት ያለው የእውነት ማስተላለፊያ ነው። (ዘሪሁን፣ 2007÷261)

ተውኔት በሚቀርብበት ጊዜ ተመልካች አቋርጦ። አስተያያት መሰጠት ሰለማይችል አና በዝምታ ሰለሚከታተሉ ተመልካች እራሱን አንዲመረምር የማድረግ ሃይሉ ክፍተኛ ነው። ፈንታሁን እንግደ "የተውኔት አፃፃፍ ዘደ" ላይ ተውኔት የሰው ልጆችን የእለት ተዕለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ በጊዜ ና በቦታ ተወስኖ የሚመደረክ ታሪክ ነው። ተውኔት የሰው ልጅችን እውነተኛ ዲርጊት የሚያካትት የጥበብ ዘርፍ ነው በማለት ገልፆታል። (1999፥9)

ተውኔት በሁለት ይከፍላል። እነሱም የአጭር ጊዜ ተውኔት እና የሙሉ ጊዜ ተውኔት ናቸው።

### 2.1.2 የአጭር ጊዜ ተውኔት

አጭር ጊዜ ተውኔት ማለት አንድ ገቢር ሲኖረው አንድ ቦታ ጀምሮ አንድ ቦታ የሚያልቅ የጊዜ ለውጥ ብቻ ያለው ነው። አጭር ጊዜ ተውኔት በሰዓት ስናያው 40ደቂቃ አሰከ1:00 ሰዓት የጊዜ እርዝማኔ ያለው ነው።

አጭር ጊዜ ተውኔት ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትዕይንት ያለው ሲሆን ጊዜው ብቻ የሚቀይር ነው። ለምሳሌ ቤት ውስጥ ከሆነ ቤት ውስጥ የሚያልቅ ይሆናል፣ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሆነ ቤተክርስቲያን የሚያልቅ ነው።

### 2.1.3 የሙሉ ጊዜ ተውኔት

የሙሉ ጊዜ ተውኔት ከአንድ ገቢር በላይ ማለትም ከአንድ ቦታ ና የጊዜ ለውጥ በተጨመሪ መሰተናገድ የሚችል ከሁለት አሰከ ሶስት ሰዓት እርዝማኔ ያለው ነው። ፈንታሁን እንግደ "ተውኔት መዝገብ ቃላት ና ፍቺዋቻቸው" ላይ ሲያብራራው።

የሙሉ ጊዜ ተውኔት የሚለው ከሌሎች ዝግጅቶች ጋር ችሎ ስይኂዴድ እራሱን ተዘጋጅቶ እራሱን ችሎ የሚቀርብ የተውኔት አይነት ነው። ሙሉ ጊዜ ተውኔት የሚለው መጠርያ ከተውኔቱ ድርሰታ ከገፅ በዛቱ እና መድረክ ሲተረጎም ሊወሰድ ከሚችለው ጊዜ ርዝማኔ ጋር ያለውን ግንኙነት ከማመልከት ውጪ የተውኔቱን ዘውግ አያሳይም።(ፈንታሁን፣ 1993÷87)

## 2.2 የቴአትር ዝግጅት

የቴአትር ዝግጅት ማለት አንድ ደራሲ የተዘጋጀውን ተውኔት በመድረክ ላይ በተዋንያን በአዘጋጅ እንዲሁም በተለያዩ ቴክኒካል ባለሙያዎች አማካኝነት መድረክ ላይ የሚቀርብበት ሂደት ዝግጅት ይበላል። የዝግጅት ሂደት አንድ መድረክ ላይ የሚቀርብ ተውኔት ለማዘጋጀት የቴአትር አዘጋጅ ባለሙያው ትልቅ ሀላፊነት አለበት።በዝግጅት ወቅት ከሚያሰፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች መካከል ዋንኛው የሙያ ሰነ ምግባር እና የቴአትር እውቀት ናቸው። ሁሉም ቴአትሩን ለመስራት የተሰባሰቡ ባለሙያዎች ጥሩ ሰነ-ምግባር እና የቴአትር እውቀት ካላቸው በመድረክ የሚቀርበው የቴአትር ዝግጅት የተዋጣለት ሊሆን ይችላል። ደበበ ሰይፉ ሰለዝግጅት አሰፈላጊነት እንዲህ ብለዋል። "የቴአትር ጥበብ ምሉዕ የሚሆነው መደበኛ መልኩንም አገኘ የሚባለው በመድረክ ዝግጅት አማካኝነት ነው።" (1973÷14)

## 2.3 የአዘጋጅ ምንነት

የቴአትር አዘጋጅ ማለት በፀሀፊ-ተውኔቱ የተዘጋጅውን ተውኔት መድረክ ላይ ህይወት ዘርቶ እንዲቀርብ የሚያደርግ ባለሙያ ነው።ይህ ባለሙያ ተዋንያንን መልምሎ፣ቃለ-ተውኔት አሰጠንቶ እና በመድረክ ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ በማስቻል ተውኔቱ እስከ ሚቀርብበት ቀን ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል መስራት ይኖርበታል። ናኦድ ጋሻው "የፊልም ጥበብ" በተሰኘው መፅሐፍ ውሰጥ ሰለ አዘጋጅ አንዲህ አስቀምጧል።

> *አዘጋጅ (ዳይሬክተር) ለህይወት ያለው ሃሳብ ሰፋ ያለ መሆን አለበት። የግል ህይወቱን ከሚመራበት ማህበረሰባዊ፣ ግለሰባዊ፣ሃይማኖታዊ እውነትና እምነት ውጪ የሌላቸውን*

*እውነትና እምነት መርምሮ የሚያውቅና ነገሮችን በብዙ አቅጣጫ የሚያይ ሰፋ ያለ ሰው መሆን አለበት። (ናኣድ፣1997÷40)*

የቴአትር አዘጋጅ ከባድ ስራና ከፋተኛ ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ በተፈጥሮ ንቁ፣ብልህና ታታሪ እንዲሁም የኪነ ጥበብ ሚስጥር የተረዳ፣የማሰተዳደር ችሎታ ያለው፣ ለሰራው ግልፅና የሙያውን ስነምግባር በተግባር የተካነ መሆን ይኖርበታል።

## 2 3.1 በዝግጅት ወቅት የአዘጋጅ ሀላፊነት

አንድ የቴአትር አዘጋጅ የተፃፈውን ተውኔት በመድረክ ለመተርጎም በመጀመሪያ የተውኔቱን ጭብጥ፣ የቃለ-ተውኔት አደረጃጀት፣ የገፅ-ባህርያት ቁጥር እና አስፈላጊነት፣ መቼቱን እና ሴራውን በተገቢ መንገድ መፃፉን ማረጋገጥ አለበት። ይህ በተመለከተ ፈንታሁን እንግድ "ዝክረ-ተውኔት" የተሰኘው መፅሃፍ ላይ እንዲህ አስቀምጠዋል።

*መሪዛ ተውኔት የተውኔቱን ድርሰት ካነበበ በኋላ ተዋንያንን በመመልመል የሚጫወቱትን ሚና በመደልደል እና ቀጥሎም ቃለ-ተውኔቱን በቃላቸው እስከ እንቅሰቃሴያቸው በማጥናት እንዲሁም ሌሎች የዝግጅት አላባውያን ማለትም ግብዐተ-ድምፅ፣መብራት፣ አልባሳት፣ ቁሳቁስ የመሳሰሉትን በመጨማመር በመድረክ ይተረጎማል። (1990÷135)*

ተዋንያን ከተመረጡ በኋላ የንባብ ልምምድ ይጀመራል። ተዋንያን የቃል ጥናት ከጨረሱ እና ገፅ-ባህርያቱን ከተላበሱ በኋላ መድረክ ላይ በእንቅስቃሴ ይሰራል። መድረክ ላይ መካተት ያለባቸውን የተለያዩ እንቅሰቃሴዎች እና ድርጊቶች በተለያየ ጊዜ በመጨመር ቴአትሩ ለተመልካች እይታ እንዲቀርብ ብቁ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ አዘጋጅ ተዋንያንን ያሰራል።

ቴአትር ለተመልካች የሚቀርብበት ጊዜ ሲደርስ ተዋንያን ከተዘጋጁላቸው አልባሳት፣ ገፅ-ቅብ፣ የመድረክ ግንባታ፣ቁሳቁሶች፣መብራት እና ግብዐተ-ድምፅ ጋር በመዋሀድ ልምምድ ያደርጋሉ። ከዛም መስተካከል ያለባቸው ቴክኒካል ችግሮች ተስተካክለው ቴአትር የሚቀርብበትን ቀን አዘጋጅ ይወሰናል። በመጨረሻም አዘጋጅ ማስታወቂያዎች አዘጋጅቶ ለተመካች እይታ ያቀርባል።

## 2.4 የዝግጅት አላባውያን

### 2.4.1 የመድረክ ግንባታ

የመድረክ ግንባታ አንድ ቴአትር ሳቢነት ኖሮት ለተመልካች እንዲቀርቡ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል። የመድረክ ግንባታ ገፅ-ባህርያት የሚኖሩበት አካላዊ ቦታ ነው። በመድረክ ላይ ለመገንባት የማንችለውን እንደ ገላጣ ሜዳ፣ወንዝ፣ዛፍ፣ቤት፣ ተራራ የመሳሰሉትን በደራዊ ቅብ አዘጋጅተን በመድረክ ላይ እናቀርባለን።

### 2.4.2 ቁሳቁስ

የመድረክ ቁሳቁስ የምንላቸው ለቴአትር የሚያሰፈልጉ መድረክ ላይ የምናሰቀምጣቸው እና በገፅ-ባህርያት የሚያዙ እቃዎችን ያጠቃልላል። ሳሙኤል ተስፋዬ "የመድረክ ጀርባ ጥበባት" ሰለቁሰቁሰ እንዲህ አስቀምጧል።

> *ቁሳቁስ በዕይታ ውሰጥ እጅግ ገዝፍ የሆነ ሚና ሊጫወቱ ይችላል። ይህን ሚና የሚጎናፅፍ ግን በዕውቀት የተደራጁ እንደ ሆነ ነው። ባማያስፈልጉ ቦታዎች የሚደነቀሩ ከሆኑ ግን ስጥቅማቸው ጉዳታቸው ያመዝናል በአጠቃላይ የመድረክ ና የተውኔት አቅርቦቱን ውድቀት ሊያፈጥት ይችላሉ። (ሳሙኤል፣ 2012÷121)*

### 2.4.3 መብራት

የመድረክ መብራት ተመልካቾች በመድረክ ላይ ያሉትን ማንኛውም ነገሮች እንዲያዩ ያስችላል ። ሳሊ ማክ "ፕራክቲካል ቴአትር" ሰለ መብራት እንዲህ አስቀምጧል። የመድረክ መብራት አላማ ተመልካቾች በፈለጉት ርቀት ላይ ሆነው የሚቀረበውን ቴአትር እንዲመለከቱ ወይም በጨለማ አዳራሽ ውስጥ ሆነው ትኩረታቸውን ወደ መድረክ እንዲያደርጉ ይገደል። (ማክ፣ 1997÷290)

የመድረክ መብራት አጠቃላይ የተውኔቱን ድባብ ይገልጻል። ለምሳሌ ተውኔቱ ጊዜ ቀን ወይም ምሽት መሆኑ የሚታወቀው በመብራት አማካኝነት ነው። ቢጫ መብራት ስንጠቀም የተውኔቱ ጊዜ ቀን ላይ መሆኑን ሲያመለክት ሰማያዊ መብራት ስንጠቀም ደግሞ ምሽት ወይም ለሊት መሆኑን ተመልካቾች ያለምንም ማብራሪያ እንዲገነዘቡ ያስችላል። ሌላው የመድረክ መብራት ገቢር በማይቀየርባቸው ከትዕይንት ወደ ትዕይንት ለመሸጋገሪያ ይጠቅማል።

## 2.4.4 አልባሳት

የቴአትር ስራ ውስጥ አልባሳት የምንላቸው በተዉኔት ውስጥ ማንኛውም ገፅ-ባህርያን ወክሎ የሚጫወት ሰው ለልብስነት የሚጠቀምበት ማንኛውም ነገሮችን ያጠቃልላል። አልባሳት የገፅ-ባህርያትን የማህበራዊ ኑሮ ደረጃ መሳሪያዎች ናቸው። ሳሙኤል ተስፋዬ "የመድረክ ጀርባ ጥበባት" ስለአልባሳት እንዲህ አስቀምጧል።

> *ቀደም ብሎ የአልባሳት ድርሰቱ ተዘጋጅቶ የአንደንዱ አልባሳት ንድፍ ተስሎ ዝርዝር መግለጫው ተዘገጅቶ ተሰናዶ ለአዘጋጅ መቅረብ አለበት። እነዚህ ቀደም ብለው ከተዘጋጁ የተውኔቱ የአልባሳት ልምምድ ጊዜ ከመድረክ በፊት አልባሳቱ በሙሉ ቀርበው፣ ተዋንያን መስተካከል ያለባቸው ተስተካክለው ለሚፈለገው ጊዜ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በአልባሳት ልምምድ ወቅትም የሚፈጠሩ ችግሮች ካሉ በፋጥነት አርሞ ለዋና የቴአትሩ አቅርቦት ዕለት ያለእንከን ለማቅረብ ዕድል ይሰጣል። (ሳሙኤል፣ 2012÷121)*

## 2.4.5 ገፅ-ቅብ

ገፅ-ቅብ ማለት በአልባሳት መሸፈን ወይም ማሳየት ያልቻልነውን ገፅ-ባህርያት እድሜ፣ የጤና፣ ሁኔታ፣ ድካም፣ ብርታት፣ የጠባሳ፣የቁስል የመሳሰሉትን ሁኔታዎችን ለማሳየት የምንጠቀምበት አንዱ የዝግጅት አላባውያን ነው። ገፅ-ቅብ ተዋንያን ገፅ-ባህርያቸውን ሆነው እንዲተውኑ ይረዳል። ሳሙኤል ተስፋዬ "የመድረክ ጀርባ ጥበባት" ስለገፅ-ቅብ እንዲህ አስቀምጧል።

> *ገፅ-ቅብ የሰው ፊት ቅርፅ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ጥበብ ነው። ከሰሙም መረዳት እንደሚቻለው የሰው ፊት ላይ የሚሰራ ጥበብ ገፅ-ቅብ ይባላል። የገፅ-ቅብ ባለሙያ ለአንድ ቤተ-ተውኔት እጅግ አሰፈላጊ ጥበብ ነው። ይሁን እንጂ አንድ የመድረክ ተዋናይ የገፅ ቅብ ስልጠና ሊያገኝና ክህሎቱን ሊያዳብር ይገባዋል። ይህን ጥበብ ማወቅ ለተዋናይ የግዴታ ያህል አሰፈላጊ ነው። ምክንያቱም ተዋንያን በተደጋጋሚ የመድረክ ተውኔት ለመስራት ወደ መድረክ መምጣታቸው የተለመደ በመሆኑ ራሳቸውን በራሳቸው የገፅ-ቅብ ስራን ለመሥራት ቢችሉ ተመራጭ ነው። አንድ ተዋናይ ከትወና ክህሎቱ እኩል ባለው ተክለ ሰውነት በአልባሳቱና በገፅ ቅብ የሚባሉትም ፋውንዴሽን ፣ፓውደር፣ሰው ሰራሽ ቅንድብ፣ሰው ሰራሽ ጢምና ፅጉር ወ.ዘ.ተ ናቸው።(2012÷168)*

### 2.4.6 ግብዐተ-ድምፅ

ግብዐተ-ድምፅ ማለት ቴአትሩ መድረክ ላይ በሚቀርብበት ጊዜ የሚገቡ የተለያዩ ሙዚቃ እና ድምፆችን ይወክላል። ግብዐተ-ድምፅ የቴአትሩን ጊዜ፣ ወቅት፣ ድባብ፣ የገፀ ባህርያትን የተለያዩ ሰሜቶች ማለትም የፋርሀት፣የደስታ እና የመሳሰሉትን የምንገልፅበት አለባውያን ነው። ግብዐተ-ድምፅ በቴአትር ላይ በተግባር ማሳየት ያልቻልነውን ድባብ ማሳያ ነው። ለምሳሌ የጥይት ድምፅ፣ የስልክ ድምፅ፣ የመኪና ድምፅ ፣የጥሩባ ድምፅ፣የእንስሳት ድምፅ እና ሌሎችንም በቴአትር ላይ ቢያስፈልግ በግብዐተ-ድምፅ አማካኝነት ቴአትሩ ሙሉ አድርገን እንድናሳይ ይጠቅመናል። ሌላው ከገቢር ወደ ገቢር እና ከትዕይንት ወደ ትዕይንት ለመሸጋገሪያ መጠቀም እንችላለን። ሳሙኤል ተሰፋዬ " የመድረክ ጀርባ ጥበባት " ስለ ግብዐተ-ድምፅ እንዲህ አስቀምጧል።

> *ግብዐተ-ድምፅ የሚባለው ንግግርም መዚቃም ያልሆነ በርካታ ሰሜቶች እና ሁነቶችን መግለፅ የሚችል ድምፅ ነው።የድምፅ ንድፉ ባለሙያው ጥንቃቄ አድርጐ ሊታሰብበት የሚገባውና አዘጋጁም በትኩረት ሊያየው የሚገባው የድምፅ አይነት ግብዐተ-ድምፅ ነው።* *(2012÷161)*

## 2.5 የተዛማች ጥናታዊ ፅሁፍ ቅኝት

ሄለን ገ/ስላሴ 2009 “ግራር ቴአትር ከፅፈተ ተውኔት እና ከ ዝግጅት አላባዊያን አንፃር “ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ለባችለር አርት ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ሲሆን ግራር ቴአትር ከፅፈተ ተውኔት እና ከ ዝግጅት አላባዊያን አንፃር ይተነተናል። ጥናታዊ ፅሁፉ አጥኚው ከሚያጠናው ጥናታዊ ፁሁፍ ጋር አንድነት እና ልዩነት ያለው ሲሆን አንድነቱ ሁለቱም ጥናቶች ስለ ዝግጅት አላባዊያን በቂ ትንተና ለማቅረብ ሞክሯል። ግራር ቴአትር ከ ፅፈት ተውኔት እና ከዝግጅት አላባዊያን አንፃር ከተሰራው ጥናት ውስጥ ስለ መብራት ፣ መድረክ ግንባታ ፣ግብዓት-ድምፅ ፣አልባሳት እና ገፅ ቅብ አንፃር የዳሰሰ ሲሆን አጥኚው እነዚህን ሃሳቦች በጥናቱ ውስጥ ለማካተት ሞክሯል። ጥናቱ አጥኚው ከሚያጠናው ጥናት የሚለየው ደግሞ ይህ ጥናት ግራር ቴአትርን ከፅፈት ተውኔት አንፃር የተሰራ በመሆኑ ሰፋ ያለ ሃሳብን ስለሚያጠቃልል ነው ።

አጥኚው ሌላ እንደ ተዛማች ፅሁፍ አድርጎ የተጠቀመው ፌቨን ዳንኤል “ባልቻ አባ ነፍሶ ቴአትር ከዝግጅ አንፃር” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ። ይህም ጥናታው ፅሁፍ ለባችለር አርት ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ሲሆን ሁለቱም ጥናቶች ከዝግጅት አላባዊያን አንፃር የተሰራ ይሁን እንጂ ጥናቱ አንድነትም ልዩነትም አላቸው። ጥናታዊ ፅሁፉ አጥኚው ከሚያጠና ፅሁፍ ጋር ያለው አንድነት ሁለቱም ስለርዕሰ ጉዳዩ ግንዛቤ ሰተዋል። ይህም ማለት ፌቬን ባጠናቸው ጥናት ውስጥ ስለዝግጅት አላባዊያን አንፃር ለመተንተን ሞክራለች አጥኚው በሚያጠናውም ይህን ርዕሰ ጉዳይ ለመተንተን ችሏል። ልዩነቱ ደግሞ ሁለቱም ከዝግጅት አንፃር መዳሰሱ እንዳለ ሆኖ አጥኚው በተጨማሪም የዝጅቱን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን ለማየት ሞክሯል።

ተስፋዬ ፍቃድ 2013 “ሚስጢሩ ቴአትር ከዝግጅት ቴክኒክ አንፃር “ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ። ይህም ጥናታዊ ፅሁፍ በተመሳሳይ ለባችለር አርት ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን አጥኚው ከሚያጠናው ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር አንድነት እና ልዩነት አለው ። አድነቱ በጥናቱ ውስጥ ስለ ዝግጅት ቴክኒካል አንፃር አቀራረቦችን ይዳስሳል። አጥኚውም እነዚህን ርዕሰ ጉዳዬች በጥልቀት ለመተንተን ሞክሯል። ልዩነቱም በአንድ ከዝግጅት ቴክኒክ አንፃር ብቻ የተወሰን ሲሆን አጥኚው የሚያጠናው ጥናት ግን ከዝግጅት አላባዊያን አንፃር ጠንካራ እና ደካማ ጎኑንም አንስቶ ለመተንተን ሞክሯል።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3 የመረጃ ትንተና

### 3.1 ሚስጥሩ ቴአትር ጭምቅ ታሪክ

ታሪኩ የመጀምረው ከወይዘሮ ብርቁ ቤት በረንዳ ላይ የሰፈር ወጣቶች አረቄ እየጠጡ በግራና በቀኝ ተቀምጠዋል። አዝማሪው እና ሚስጥሩ ከተቀመጡት ወጣቶች ፊት ለፊት ተቀምጠው አዝማሪው ማሲንቆውን እየመታና ሚስጥሩ ግጥም እያወረደ የተቀመጡትም ሁለቱ የሚስጥሩ ጓደኞች እያጨበጨቡ ሚስጥሩም የጎጃም እስክስታ ይመታል። በሌላ ጎን የተቀመጡት የሚስጥሩ ባላንጣ የሆኑት ሶስት ወጣቶች አንገታቸውን ደፍተው በንዴት ተቀምጠዋል።

አይቺ ከሚስጥሩ ጋር በፊት ፅብ ሰለነበረው ሚስጥሩን ሲያየው ተመልሶ ሊወጣ ሲል አብሮት የመጣው ባቼ እንዳይወጣ ይይዘዋል። ከዚያም ከሶስቱ ጓደኞቻቸው ጎን ይቀመጣሉ አረቄውንም በንዴት እያስቀዱና ደጋግመው እየጠጡ ሚስጥሩን ይመለከታሉ። አዝማሪውም ከሚስጥሩ ጋር ይጫወታል። አይቺ እና ባቼም አዝማሪውን እንዲያጫወታቸው ይነግሩታል። አዝማሪው ሚስጥሩ ከጎኑ ሰለቆመበት ወደ ሚስጥሩ ዙሮ ማሲንቆውን አየመታ ይጫወታል። አይቺ እና ባቼም በንዴት “በል ደግሞ ተቀበል እንጂ ንቀት ነው” እያሉት አሁንም ወደ ሚስጥሩ ዙሮ ይጫወታል። አይቺም በንዴት “አታጫውተንም እንዴ” ብሎ ሲነሱበት ወደ እነሱ ዙሮ ይጨወታል።ሚስጥሩ ከሁለቱ ጓደኞቹ ጋር ሄዶ ይቀመታል።አዝማሪው "ሆይ መላ ንሽ አሉ ሆይ መላ" ሲል አይቺ “የምን መላ ነው የምትለው አያ በለዉ በለው ብለህ” ተጫወት ይለዋል። አዝማሪው አያ በለው በለው በማለት ይጫወታል። አያ በለው በለው ማለት እና ግጠመኝ እንደ ማለት ሲሆን ሚስጥሩ ተንኮል እንዳሰበ ይገባው እና አይቺ ቁጭ ብሎ አረቄውን እየጠጡ እስክስታ እየመቱ አብረው ይዘፍናሉ። ከዚያም የሚስጥሩ ወንድም አያሌው ጓደኛው ጣፈጠ ይገባሉ። አያበለው በለው የሚለውን ዘፈን ሲሰሙ ጣፈጠም ፈርቶ እኔ ጠብ አልወድም እንሂድ ይለዋል። አዝማሪውም አይቺን ማጫወት ይጀምራል ከዚያም አንዱ ተንስቶ ድንገት ተቀብሎ "ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል "ሲል ይስቃሉ ሚስጥሩ እየሳቃ "ወተቱ ቢሸፍት ታገፍቶ ተገናፍቶ ቂቤ ይወጣዋል በገዛ እጅ ሰፍቶ" ጓደኞቹው ይስቃሉ። እነዚያኞቹም ተነስተው ተራ በተራ ይተራረባሉ።

በመጫረሻ ላይ ደግሞ በሚስጥሩ ሞት ምክንያት የአካባቢው ማህበረሰብ በጡሩንባ ለፍላፊ ይነገራል በዚያም መሰረት አካባቢው ከሚገኝበት ዋርካ ስር ወጣቶች፣ አባቶች፣ እናቶች፣ ሽማግሌዎች፣ ቄሶች፣ መሪጌታ፣ ፀሐፊ ተዕዛዝ እና መሳርያ ያለቸው ጥበቃዎች ይገኛሉ።

ከዚያም በኋላ ወደ ባህልዊ የዳኝነት ስነ-ስርዓት ይገባሉ።ሁለት ጥይት የተቀባበለ መሳሪያ በማጋደም ወደ ፍርድ ሂደት ይገባሉ። ይህኛው ቢስተኝ ያኛው አይሳተኝ እያሉ አንዲዘሉ ይታዘዛሉ።ተጠርጣሪዎቹ በፍርሃት አንድ በአንድ የተጋደመውን መሳሪያ ይዘላሉ በስተመጨረሻም ልጁ በብር እጦቶ የሞተችበት አያ በላይ በፍርዱ ሂደት በመናደድ እሱ እንደገደለው ና ቤቱን እንዳቃጠለ ተናግሮ ወንጀለኛው ይያዛል።

በሚስጥሩ ሞት ማጣራት ውስጥ የሚስጥሩ እሰከዛሬ የሀገርን ሀብት ሲሸጥ የሰውን ገንዘብ እየሰረቀ እያስቀመጠው በሳጥን ግማሹ ተቃጥሎ ግማሹ ሳይቃጠል ይገኛል።

## 3.2 የዝግጅት ወቅት

በዝግጅት ወቅት መጀመሪያ ንባብ ቴአትሩ እስከሚቀርብበት ጊዜ ውስጥ ያለቸው ቴክኒካል ልምምዶች ናቸው።በመጀመሪያ የተዋናይ መረጣ በሚድረግ ታሪኩን ለሚያራምዱ ተዋንያን የፅሁፍ ተውኔቱን በመስጠት ገፀ ባህርያቸውን በጥልቀት በመተንተን እንዲረዱ እንዲሁም ቃለ ተውኔታቸውን እዲያጠኑ የሚደረግ እና አጠቃላይ የተውኔቱን አባላትን ሰብስቦ ስለ ተውኔቱ አጠቃላይ ሁኔታውን ስንመለከት ሁሉም ተዋንያን ፅሁፍ ተውኔቱ አጥንቶ በመገኘት በቀጥታ ወደ መድረክ እንቅስቃሴ ጥናት በመግባት እግር መንገደቸውን ቃለ ተውኔቶቻቸውን እያጣሩ እንዲሄዱ የሚያደርግ የዝግጅት አካሄድ ተጠቅሟል። በዚህ በዝግጅት ወቅት ውስጥ የነበረውን የልምምድ ሂደቶች ስንመለከት አዘጋጁ ተስፍዬ ገ/ማርያም በሚፈልገው መልኩ ተዋንያን እየታዩ በተለያዩ ጊዜ በማግኘት ሲያዘጋጅ የነበረበትም ሁኔታ ነበረ። ይህም ማለት አጀብ ተዋንያኖች ለብቻ በመቅጠር ማለማመድ ተዋንያን በሌላ ሰዓት በመገኘት ገፀ ባህርያቸውን በሚገባ እንዲወሃዱ የማድረግ ስራ እንዲውም ታሪኩን የሚያራምዱ ሌሎች ገፀ ባህርያትንም ለብቻቸው በማግኘት ስለስራችው በሚገባ እንዲያውቁት ስራቸው ያለው እንደሆኑ ዘንድ ተገቢውን የዝግጅት ግብዓት እንዲያገኙ ና ልምምድ አንዲያደርጉ ተደርጓል። የዝግጅት ወቅት የመጨረሻ ምዕራፍ የሚሆነው የአልባሳት የዝግጅት አላባውያንን አጠቃላይ

ተውኔቱ የሚፈልገውን ግብዓት ተጠቅሞ ልምምድ የሚደረግ ሂደት ሲሆን ይህንን ሚስጥሩ ተውኔት ለስምንት ያህል ተግባራዊ አደርገውታል። የዝግጅቱ አስተባባሪ ንጉሴ ባይሌ በዚሁ መልኩ በስልክ ቃሉን ሰቷታል።

## 3.3 ሚስጥሩ ቴአትር ቅርፃዊ እና ይዘታዊ አቀራረበ

### 3.3.1 ቅርፃዊ አቀራረብ

ሚስጥሩ ቴአትር ከቅርፅ አንፃር በሁለት ገቢር እና በሁለት ትዕይንት የተዋቀረ ሲሆን በተውኔቱ ዕሁፍና መድረክ ላይ ትዕይንቶች መቀየራቸው የሚገልፅው በመብራት መጥፈት ኣና መብራት ነው። በመሆኑም በመጀመሪያው ገቢር አንድ ትዕይንት አንድ ላይ መብራት በማጥፋት ይጠቀማል። ገቢር አንደ ትዕይንት አንድ የሚሰጠውን የሚስጥሩ ወንድም አያሌው ሚስጥሩ ከአይ በላይ የተበደረውን ብር እንዲመልስ በአፋጣኝ ስላስጠነቀቀው ነው። በመጀመሪያ ትዕይንት ሲጀመር እንደጨለማ አዝማሪው ድምፅ ና አረቄ የሚልየሰው ድምፅ ሰንሰማ መጣጥፍ ቤት መሆኑን እንረደለን።

ገቢር ሁለት ትዕይንት አንድ ሲጀምር ደግሞ መብራት ሲይበራ የእሳሳቶች፣የጡሩንባ ፣ የወፎች ድምፅ ስንሰማ እየነ መሆኑና የጊዜ መለወጡ የሚያመለክት ነው። ተውኔቱ ትውፍታዊ ሲሆን በውስጡ ህብረ ዝማሬን እና ባህላዊ ጭፈራን የሚያካትት ሲሆን መድረክ ላይ ቆይቷል። 2:15 ርዝመት ያለው ኮርሶች እና ዋና ተውንያያች ጨምሮ 49የሚሆኑ ገፅ-ባህርያት የያዘ ነው።

### 3.3.2 ይዘታዊ አቀራረብ

ሚስጥሩ ቴአትር ከይዘቱ አንፃር ስንመለከት ርዕሰ ጉዳዩን ባህል ላይ ያደረገው ይህ ተውኔት ውሸት ተደብቆ እንደማይቀር የሚያስገነዝብበት ነው። ተውኔት ውስጥ እንደሰፈረው ሚስጥሩ አይቼ የሚወዳትን ሚስት በማግባቱ ምክንያት ይጋጫሉ።ከዚያም ሚስጥሩ ጉዳዩ ሳይታወቅ ይሞታል። በጎጃም ባህል መሰረት አንደ ሰው በሰው እጅ ነፍስ ከጠፋ ዕርቅ ሰላም እንዲወርድ አካባቢውን ማህበረሰቡን የገደለውን ሰው በማጠራት በዚህ ሁለት ጎራ የሀሳብ ፍልሚያ ውስጥ ብዙ የመፍትሄ ሀሳቦች የሚነሱ እና የሚወደቁ ሲሆን የማህበረሰቡ ሰዎች በንዴት ፣ ጭንቀትና ፍርሃት ጉዳዩ በማጋለጥ ችግሩ ይፈታሉ።

## 3.4 ተውኔታዊ ድርጊያው

ሰለተውኔታዊ ድርጊያው ምንነት በውስጡ ሰለሚያካትቷቸው ሚሰጥሩ ተዉኔት ደራሲው የታሪኩ ቦታ፣ ጊዜ ማህበራዊ እውነታን የምንገነባቸው መንገዶች እርስ በርሳቸው የሚያደርጉት ንግግር ማወቅ ይቻላል። ገቢር አንደ ትዕይንት አንድ ላይ ወጣቶቹ ተሰባስበው አረቄ እየጠጡ የሚያነሳሳቸው የግጥም ቅኔ እና የአነጋገር ዘያቸው ይነግረናል። ገቢር ሁለት ላይ ትልቅ ዋርካ ስር ሹማግሌዎች እና ወጣቶች ተሰብስበው ወንጀለኛውን ማውጣት የሚረጉ መሆኑን ይነግረናል። ለምሳሌ በመጀመሪያ ገቢር እና ትዕይንት ፦

አባይ ሲይፈርሰ ሲመስል እንቆቆ

ገራጣው ጎጃሜ መጣ በአጭር ታጥቆ

ከዚህ ላይ እንደምንረዳው በገፀ ባህርያት ቃለ ተውኔት መሰረት ሚስጥሩ አጠቃላይ ተውኔታዊ ድርጊያዊ ጎጃም ማህበራሰብ ውስጥ እንደሆነ እንመለከታለን።

## 3.5 ድባብ

ገቢር አንድ እና ትዕይንት አንድ ላይ ሚስጥሩ በጣም ተንኮለኛ በመሆኑ ነገሮችን ሁሉ የሚፈፅመው በድብቅ ነው። ሚስጥሩ የሀገርን ቅርሶች አሳልፈ ለነጮች የሚሸጥ ሲሆን በአካባቢው ወጣቶች ና አባቶች አይወደድም። የአካባቢው ወጣቶችም ሚስጥሩ ወደ የሚገባበት መጠጥ ቤት አየገቡ የሸጣቸውን የሀገራቸውን መሬት፣ ንዋዩ ቅዱሳን በሮችን በመዝረፍ እና የተለያዩ ቅርሶችን በመሸጥ ብሎም የአካባቢው ሴቶች ከባሎቻቸው እያፋታ የሚያገባ ሲሆን የአካባቢው ወጣቶችም እሱን ለመግደል የማያደርጉት ጥረት የለም ከዚያም ፀብ ይፈጠራል። ከዚህ ላይ የምንረዳው የንዴት፣ የብስጭት፣የሀዘን፣ የግድያ ድባብ እናየለን። ከዚህ ትዕይንት የምንመለከተው ትኩረት እንድንሰጠ የሚያደርግ በመሆኑ አጥኚው ይህን እንደ ጠንካራ ጎን ወስዶታል።

## 3.6 የዝግጅት አላባውያን ትንተና

### 3.6.1 መድረክ ግንባታ

ሚስጥሩ ቴአትር የገፅ ግንባታ ይዞታውን ስንዳስስ ሰለ ቴአትሩ ዘወግ ሰለ ገፅ ባህርያት ምንነት እንዲሁም መቼቱን መመልከት ብቻ የምንገምተውና የምንረዳው ነው። ድባቡን ለመግለፅ ከመድረክ በተመልካች ፊት ለፊት ከትልቅ ዋርካ ዛፍ ፊት ለፊት

ማህብረሰብ ተሰብሰቦ ይታያል። ከጎጆ ቤት ፊት ለፊት የተደረደሩ በርጨማ ወንበሮች ላይ በግራና በቀኝ ሰዎች ታቀሚቶ አሪቂ ይጠጣሉ። ዋርካ ዛፍ በጣም ግዙፍ ከመሆኑ የተነሳ ፊት ለፊቱ ያለችውን ጎጆ ቤት ከላይ አልብሷታል። ትዕይንት ሁለት የእርቅ ስነ ስር ዓቱ የሚከናወነው በትልቅ ዋርካ ስር ነው ። ከዋርካው በተመልካች በቀኝ በኩል ሶስት ከፊ ከፊ ያሉ በእንጨት የተሰሩ ወንበሮች ይገኛሉ ።ከዋርካው መሀል ሁለት የእንጨት ወንበሮች ይገኛሉ።ምክኒያቱም የገጠር ባህላዊ የዕርቅ ስነ-ስርዓት ሲካሄድ ዳኞች በሁለቱወንበሮች ላይ ተቀምጠው ወንጀለኛውን ለፍርድ የሚያቀርቡበት ነው ።አጥኝው ይህን እንደ ጠንካራ ጎን ወስዶታል።

### 3.6.2 ግብዓተድምፅ

ሚስጥሩ ቴአትር ላይ ግብዓተ ድምፅ ስንመለከት በብዛት ቴአትሩ ስሜት የሚገልፅ የአሰደንጋጭና ጊዜውን የሚገልፅ ደምፀት ተጠቅሞ የምንናኘው ሲሆን በትንታኔ ለመመልከት ያህል ቴአትሩ በዋናነት ፀብ የሚበዛበት ታሪክ ያለው በመሆኑ የገፀ ባህሪያቱን አሳዛኝ አስደንጋጭ፣ አስፈሪ፣ግድያ እና ሌላ ድርጊቶች ተመሳሳይ ስሜቶች ባላቸው ድምፆች ደግፎ በማጉላት ፣ ለመሸጋገርያነት እና የጊዜውን ሁኔታ ለማሰወቅ እንዲያስችል ከብቶች ጩኸት፣ የጡሩባ ድምፅ ና አስፈሪ ንጎድጎደ ድምፅን የሚወክል ግብዓተ-ድምፅ ተጠቅሟል።አጥኚዊ ግብዓተ-ድምፅን እንደ ጠንካራ ጎን ወስዶታል።

### 3.6.3 መብራት

የመብራት ስርጭት የቴአትር አጠቃላይ እይታ ወሳኝነት ያለው ነው። የሚስጥሩ ቴአትር የመብራት አጠቃቀም ስንመለከት በትንሹ መጠነኛ እይታ የሚፈጥር ደብዛዛ እየፈካ የሚሄድ መብራቶች የመጀመሪያው ትዕይንት ሲከፈት የሚጠቀም ሲሆን ደባቡ ለማጉላት ውስጥ የተለያዩ ስሜቶች ለመደገፍ ሲባል የተደረገ ነው። በዚህ ቴአትር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ መሠረቶችን ና ምክኒያታዊነትን ስንተነትን የአትኩሮት መብራት አንድ ትኩረት እንዲሰጥበት ለፈለግነው ነገር ወይም ዋና ገፅ ባህሪ የምንጠቀምበት ሲሆን ከአጠቃላይ መድረክ ይልቅ እይታ እንዲያገኝ የምንፈልገውን ቦታ ወይም ገፅ ባህሪ ለይተን የምንለይበት የመብራት አይነት ነው። የቀለማቱ ልዩነትና ትርጓሜ በተመለከተ ሚስጥሩ ቴአትር ኢ መሪር (ኮሜዲ) ዘውግ ያለው ሲሆን ሙሉ የመድረክ መብራት ከስሜት ነፃ የሆኑ እይታ ለመፍጠር ተጠቅመዋል።አጠቃላይ መብራት ስርጭት ስንመለከት ጭጋማ እና ጠንካራ ጎን ይታያበታል። ምክኒያቱም ብዙ ጊዜ ሙሉ የመድረክ መብራት ብቻ ይጠቅመሉ። ነገር ግን ነጥብ መብራት

ልጣቀሙ  ይችሉ ነበር ። ጠንካራ ጎን ደግሞ መጨረሻ ትዕይንት ላይ አይ በላይን አያሌው ግሩን በጥይት ሲማታ ጊዜ  ነጥብ መብራት የተጠቀሙትን አጥኚዊ እንደ ጠንካራ ጎን ብሎ ወስዶታል።

### 3.6.4 ቁ ሳ ቁ ስ

በሚስጥሩ ተውኔት ላይ የተለያዩ ቁሳቁሶች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን ታሪኩን ለማሟላት አይነተኛ አስተዋፅኦ ያለው ነው። የቁሳቁሶች አይነተኛ ጠቀሜታ ስንመለከት ከተንቀሳቃሽ ቁሳቁሶች ሰንጀምር ቴአትር ትውፊታዊ እንደ መሆኑ ዘወትር ከብሔረሰቡ አካላት እጅ ላይ የማይጠፉ መገልገያ የሚሆኑ በትሮች ፣ ጥይት ፣ጥርስ መፋቂያ እና እንዲሁም ወጣቶች በሚንቀሳቀሱበት ሰዓት ይዘውት የሚቀሳቀሱት  በትሮ  ናቸው። ሌላው ማሲንቆ አዝማሪው የተጠቀመበት ሲሆን ጡሩንባ ደግሞ አካባቢ ዕድር ለፋፊ በእርቅ ሰዓት ፀጥታ ያስከብሩበታል ። ሌላው መሳሪያ ሲሆን መሳርያውም የአካባቢውን ዕጥታ ለማስጠበቅ እርቅ ሰላም በሚኖርበት ሰዓት ፍርድ ሲፈርድ መሳሪያውን አግድም መሬት ላይ በማስተኛት በመዝለል ፍርድ የሚከናወንበት፣ ፍርዱንም የሚያከናውኑት የቁስ ጭራ፣መሰቀል፣ደብተር፣ ቁልፍ ፣ሳጥን ፣ እስክርቢቶና ወረቀት የመሳሰሉት ነገሮች በፍርድ ውስጥ የሚገለገሉባቸው ዕቃዎቹ ናቸው። ሁለት ጥይት አሲተኝቶ"ይሄኛው ቢስተኝ ያኛው አይሳተኝ" እያስበሉ ማስዘለሉን  አጥኚዊ ይህን እንደ ጠንካራ ጎን ወስዶታል። ምክኒያቱም ወደ ዘመነዊ ዳኝነት ሰነ-ስርዓት መውሰድ ፊት ወንጀለኛውን እንዴት  ማውጣት እንደሚችል ለተመልካች ይሳያል።

### 3.6.5 አልባሳት

በሚስጥሩ ቴአትር አልባሳት ስንመለከት ተውኔታዊ ታሪኩ በኢትዮጵያ አማራ ክልል የጎጆም  ማህበረሰብ ባህል እንደሆኑ የብሄረሰቡን ትክክለኛ አልባሳት የተከተለ ነው። በመሆኑም ወጣቶች ቡኒ ከለር ሙሉ ተነፍነፍ ኮቶች እና ቀሚስ ከአንገታቸው ቀይ፣ነጭ ፎጣ ጠምጥመዋል። ከግንበራቸው ነጫጭ ሻሽ የጠመጠሙ ሲሆን  ጥቁር ሸበጥ ጫማ ተጫምተዋል። ሚስጥሩ ደግሞ ቀይ ሸበጥ ጫማ ተጫምቷል።

አይቼ ደግሞ ጥቁር ከቆዳ የታሰረ ጫማ እና ቀይ ከጨርቅ የታሰረ ኮት ለብሱእል ። አዝማሪው ደግሞ ነጭ ከጨርቅ የታሰረ ሱሪ ፣ እራሱን በነጭ ሻሽ ጠምጥሟል።አረቄ ሻጯ ወይዘሮ ብርቂ ሙሉ ነጭ የጎጃም ቀሚሱን ጥቁር ኮንጎ ጫማ ለብሰላች።

ወደ ትዕይንት ሁለት ሰንሄድ የዕርቅ ቦታው ላይ ሴቶች ከራሳቸው ጥቁር ሻሽ፣ነጫጭ የሃበሻ ቀሚስልብሰዋል፣ ጥቁር የጎማ ጫማ ተጫምቷል። ወጣቶች ከፊት የለበሱትን ይለብሳሉ። የሚስጥሩ ወንድም አያሌው ወንድሙ ሚስጥሩ ሰለሞተበት ሙሉ ተነፋነፍ ልብስ እና ከአንገቱ ላይ ጋቢ ለብሷል። ዕሁፍ ትዕዛዝ እና መሪጌታ ጥቁር ካባ፣ነጫጭ ጥምጥም እና ነጭ ጨርቅ ሱሪ የለበሱ ሲሆን ቁስ ደግሞ ከጥምጥም ጀምሮ ሙሉ ነጭ የጨርቅ ሱሪን ልብስና ጥቁር የጎማ ጫማ ተጫምተዋል። ልጅ የሞተችበት አያ በላይ ጥቁር ሱፍ ኮት በውስጥ ፣ ቡኒ ሸሚዝ፣ ቡኒ ጨርቅ ሱሪ ፣ ጥቁር ኮጎንጎ ጫማ ና ከአንገቱ ላይ ጋቢ ደርቧል። ጡሩንባ ለፋፊው ቡኒ ካፓርት ሰማያዊ ፎጣ ከላይ ለብሷል። ቫዮንጉረጉር የጠመጠመ ባርኔጣ፣ ጥቁር ሸበጥ ጫማ ተጨምተዋል። ሁለት ተጓጐች ደግሞ ሰማያዊ ጨርቅ ሱሪና ጃኬት ለብሰዋል። የአይቼ ልጅ ሙሉ አረንጓዴ ባለ ቁልፍ ሙሉ ቁሚስ ፣ ጥቁር ሻሽ ና ነጭ ነጠላ ዘቅዝቃ ለብሳለች። የሚስጥሩ እናት ሙሉ ቢጫ የመንኩሴ ልብስና ቆብ ለብሳለች።አጠቃላይ ወንዶችም ሴቶችም የተጠቀሙት አልባሳት አጥኚው ይህን እንደ ጠንካራ ጎን ወስዶታል። ምክኒያቱም የገጠር አካባቢ ባህላዊ አልባሳት መሆኑን ለተመልካች ግንዘቤ ሰለሚሳጥ በመሆኑ ነው።

### 3.6.6 ገፅ ቅብ

ሚስጥሩ ቴአትር ገፅ ቅብን በተመለከተ ባህላዊ ክዋኔውን እንዳለ ለማምጣት ወጣቶች ፀጉራቸውን ተቆርጠው ወደ ገፀ ባህሪው እንዲ ሄዱ የተደረገ ሲሆን ሽማግሌዎችም ፊታቸውን ና ልብሳቸውን የማይሸፈነውን አካላቸው ጥቁር ቀለም የተለያዩ አይነት ዲዛይን በመሰራት ያሸበርቃሉ። ሴት ተዋንያን እንደ ወንዶች ፊታቸውንና ልብስ የማይሸፍነው አካላቸውን በጥቁር ቀለም የተለያዩ አይነት ዲዛይን በመስራት ለምሳሌ የመስቀል ቅርፅ በአንገታቸው ላይ ይሰራሉ።

ሌላ የሽማግሌ አባቶች ገፅ ቅብ ሲሆን እነሱም ፀጉርና ፂማቸው ነጭ ቀለም በመቀባት ሸበት በማስመሰል ብቻ ይከወናል። ሰለሚስጥሩ ቴአትር የገፅ ቅብ ግብዓቶች ሰንመለከት በመጀመሪያ ቆዳቸውን ቅባት በመቀባት ከዚያ ላይ ጥቁር እርሳስ ቀለም እና ነጭ የጥርስ መቦረሻ ኮልጌት ተጠቅመዋል። ይህም የተጠቀሙበት ምክንያት ስናይ ሁለቱም ገፅ በቀላሉ በውሃ ብቻ የሚለቁ ናቸው።

# ምዕራፍ አራት

## 4 ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ

### 4.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ሚስጥሩ ቴአትር ውስጥ ዝግጅት አላባዊያን ትንተና አና ገለፃ ለመስጠት አድርጓል።። በተጨማሪም ጥናቱ ዝግጅት አላባዊያን ትንተና ውሰጥ ደካማና ጠንካራ ጎን ምክኒያታዊ በሆነ መንገድ ሂስ ለማድረግ አድርጓል። ጥናቱ የደሰሳቸው በአጠቃላይ ሰለዝግጅት አላባዊያን ትንተና በቂ ትንታኔን በመስጠት እረገድ ጥናቱን ለሚመለከቱ ሁሉ ጥሩ ግንዛብ መሆን ይችለል። ሚስጥሩ ቴአትር ዝግጅት አላባዊያን ትንተና ሰንደስስ መብራት ስርጭት፣ ግብኣተ-ድምፅ፣ ቁሳቁስ፣ አልባሳት እና ገፅ-ቅብ ማካተት አጥንቷል። ደረሲያንም ሆነ አንባቢያን በድክመቱም ሆነ በጠንካራ ጎኑ ጥሩ እውቀት የሚስምቱበት ጥናታዊ ፅሁፍ ሆኖ ቀርቧል።ጥናቱም እያንዳንዱ የዝግጅት አላባዊያን ጠንካራ ና ደካማ ጎን ለመጥናት ሞክሯል።አጠቃላይ የሚስጥሩ ቴአትር ዝግጅት ወቅት የነበረውን ሂደት በጥናቱ ውስጥ አስቀምቶል።

### 4.2 የመፍትሄ ሀሳብ

አጥኚው ሚስጥሩ ቴአትር ውስጥ ነበራው ሁኔታ መረጃዎችን በማጣቀስ ከዝግጅት አላባዊያን አንፃር ተንትኗል። ሚስጥሩ ቴአትር ዝግጅት አላባዊያን ያዋቀረ በሆንም እያንዳንዱን የዝግጅት አላባዊያን አንፃር ነጣጥለን ለማየት ስንሞክር ግን ክፍተቶች ይታዩበታል። ታሪኩ ለማልከቾች ስሜት በመጀመሪያው አሰከ ፍፃሜው ድረስ በጉጉት ለማየት እንዲችሉ ከዝግጅት አላባዊያን ከዚያ በላይ ቢጠነክር ያሻሉ ነበር። በተጨማሪም መብራት ስርጭት ላይ ሙሉ የመድረክ መብራት ብዙ ጊዜ ሊጠክም ነበሩ።ነገር ግን ሌላ ነጭ ነጥብ መብራት መጣከም ይችሉ ነበር። መድረክ ግንባታ ላይ ትልቅ ዋርካ ስር ቀኝ እና ግራ በኩል አጫጭር ቁጥቆቶች በኖሩ ከዚህ በላይ ለተመልካች ገጠር መሆኑን ሌሳምን ይችል ነበር።

# ዋቢ-መፅሃፍት


ሳሙኤል ተስፋዬ። ***"የመድረክ ጀርባ ጥበባት። "*** አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ፣(2012 ዓ.ም)።

ናኦድ ጋሻው። ***"የፊልም ጥበብ ።"*** አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ (1997 ዓ.ም)።

ዘሪሁን አስፊ። ***"የሰነ-ፅሁፍ መሰረታዊ።"*** **አድሳ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት ፣(2007 ዓ.ም)።**

ደበበ ሰይፉ። ***"*** የትያትር ጥበብ ።" አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣(1973 ዓ.ም)።

ፈንታሁን እንግዳ። ***" የተውኔት መዝገባ ቃለና ብያኔቻቸው።"*** *አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ፣(1993 ዓ.ም)።*

----------። ***"የተውኔት አፃፃፍ ዘይ።"*** *አድሰ* ***አበባ ንግድ ብርሃን ሳላም*** ማተሚያ ድርጅ፣(1999 ዓ.ም)።

----------። "***ዝክር ተውኔት።*** " ብርሃንና ሰላም ቤት፣ (1990 ዓ.ም)።

**አባሪ**

**ቃለ መጠይቅ**

**√ የሚስጥሩ ተውኔት የቴክኒካል ግብኣቶች አጠቃቀም ምን ይመስላል?**

**√ የሚስጥሩ ተውኔት አጠቃላይ የዝግጅት ወቅት ማለትም ከንባብ ጀምሮ ቴአትር እስከ ሚቀረቡበት ሰዓት ድረስ የነበሩ የዝግጅት አላባውያን መላቴም መብራት ስርጭት፣ ግብኣተ-ድምፅ፣ቁሳቁስ፣ አልባሳት እና ግብ-ቅብ ምን ይመስላሉ?**

**√ በዝግጅት ሂደት ውስጥ የነበረውን ሚና እና የገጠሙትን ተግድሮች ምን ይመስላሉ?**